15¾ ›mT qÜ_R 5
15th Year No. 5

ÆHR ÄR ሚያዝያ 29 ቀን 2002 ›/M
Bahir Dar 7th May, 2010

bxþT×eÃ ØÁ‰§êE ÁäK‰sþÃêE ¶pÜBlþK
yx¥‰ B¼¤‰êE KLL MKR b¤T

ZKr ÞG
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

bx¥‰ B¼¤‰êE KL§êE mNGST MKR b¤T «ÆqEnT ywÈ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ÃNÇ êU BR 2.40
Unit price

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 169 /2002 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ /እንደተሻሻለ/ እንደገና ማሻሻያ የወጣ አዋጅ

CONTENTS

Proclamation No 169/2010 The Amhara National Regional State courts Establishment Proclamation (as amended) Re-

አዋጅ ቁጥር 169 /2002 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ መወሰኛ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በሕግ የበላይነት፣ በግልፅነትና በተጠያቂነት መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No 169/2010

The Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation Re- amendment Proclamation

WHEREAS, it is found necessary to enable Courts to be efficient, effective and accessible as will best allow them to win the public trust guided by the principle of rule of law, transparency, and accountability;

የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሻለ አገልግሎት በመስጠት የሕዝብ አመኔታን ማግኘት ይቻላቸው ዘንድ አደረጃጀታቸውን፣ አሰራራቸውንና እንደተገቢነቱም የዳኝነት ስልጣናቸውን ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታው በሚጠይቀው መጠን ማስተካከል በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ /49/ ንዑስ አንቀጽ /3/ /1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ/ም " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 11/1988 /እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ እንደሚከተለው በድጋሚ ተሻሽሏል።

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ **6** ተሠርዞ

በሚከተለው አዲስ አንቀጽ **6** ተተክቷል፤

6. ስለ ፍርድ ቤቶች የስልጣን ክልል

WHEREAS, it is found necessary to adjust the organization and operation of Courts and judicial power of the region according to the economic reality requires inorder to get peopole's trust by rendering best service.

NOW, THEREFORE, in accordance with the powers vested under Article 49 (3) (1) of the Regional Constitution (as amended), the Amhara National Regional State Council hereby proclaims as follows:

1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Courts' Establishment (re-amendment) proclamation No 169/2002".

2. Amendment

The Amhara National Regional State Courts' Proclamation № 11/2006 is hereby re-amended as follows:

A. Article 6 is deleted and replaced by the following new Article 6,

"Article 6 Jurisdiction of Courts''

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር፣ በወንጀል፣ በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓትም ሆነ በሌሎች ሕጎች በተደነገገው መሰረት የሚቀርቡላቸውን ክሶች በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ ይመለከታሉ፣ፍርድ ይሰጣሉ።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቶቹ በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ /62/ እና /63/ ስር በሰፈሩት መርሆች መሰረት ይንቀሳቀሳሉ።

ለ/ <u>የአዋጁ አንቀጽ **7** ተሰርዞ በኋላ ከተሻሻለው አንቀጽ **6** ቀጥሎ ከዚህ በታች የተመለከቱት አዳዲስ አንቀጾች **7፣8፣9፣10፣11** የገቡ ሲሆን በነዚሁ ተጨማሪ አንቀጾች መካተት ምክንያት ከአንቀጽ **8** እስከ **22** ያሉት አንቀጾች ከአንቀጽ **12** እስከ **27** ሆነው ተሸጋሽገዋል</u>፣

1. The Amhara National Regional State Courts' shall have first instance and appellate jurisdiction pursuant to the powers vested to them in the civil, criminal, procedural and other laws.

2. Without prejudice to sub-article 1 of this Article, they shall exercise their power based on the principles stated under Article 62 and 63 of the Amhara Regional State Constitution.

B. <u>Article 7 is deleted and the following new Articles 7, 8 , 9, 10 and 11 are replaced while Articles 8 through 22 are renumbered as articles 12 to 27 in their order</u>,

7. ስለ ወረዳ ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የወረዳ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ስነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች ሕጎች መሰረት የሚቀርቡላቸውን ክልል-ነክ የፍትሐብሔር ጉዳዮች የመዳኘት ስልጣን አላቸው።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የወረዳ ፍርድ ቤቶች፣

ሀ/ በሚንቀሳቀስ ንብረት እስከ ብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ ብር /

ለ/ በማይንቀሳቀስ ንብረት እስከ ብር 100,000.00/ አንድ መቶ ሺ ብር/ ግምት ያላቸውን የክልል የፍትሀብሔር ጉዳዬች ለመዳኘት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ይኖራቸዋል።

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ስር የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳ ፍርድ ቤቶች ወላጅነትን ፣አካልን ነፃ ማውጣት /ሐብየስ ኮርፐስን/ እና ሌሎች የገንዘብ ግምት የሌላቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዬች የመመልከትና የመዳኘት ስልጣን ይኖራቸዋል::

Article 7. Civil Jurisdiction of the Woreda Courts'

1. Woreda Courts Shall have civil jurisdiction over regional matters pursuant to the powers vested to them in the civil procedure and other laws.

2. Without prejudice to sub article 1 of this article, they shall have first instance jurisdiction to try:

a. all suits regarding movable property where the amount involved does not exceed 50,000 Ethiopian Birr, /Fifty thousands Birr/.

b. all suits regarding immovable properties where the amount involed does not exceed 100,000 Ethiopian Birr. /One hundred thousands Birr/.

3. Without prejudice to sub articles 1 and 2 of this article, they shall exercise jurisdiction over filiation, habeas corpus and other cases the subject matter of which cannot be expressed in money.

8. ስለ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ፍትሐብሔር ነክ የዳኝነት ስልጣን

1. የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት እና በሌሎች ሕጎች መሠረት የሚቀርቡላቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ አይቶ የመዳኘት ስልጣን አላቸው።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ ድንጋጌ ቢኖርም ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በዳኝነት የሚመለከቷቸው ክልል-ነክ የፍትሐብሔር ጉዳዮች፦

ሀ/ በሚንቀሳቀስ ንብረት ከብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺ ብር/

ለ/ በማይንቀሳቀስ ንብረት ከብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ ብር/ በላይ ግምት ያላቸውን ይሆናል።

Article 8. Civil jurisdiction of the regional High Court

1. Regional High Courts shall have first instance and appellate jurisdiction pursuant to the civil procedure code and the powers vested to them by other laws.

2. Without prejudice to sub article 1 of this Article, regional High Courts shall have jurisdiction:

a. regarding movable property where the amount involved exceeds 50,000 Ethiopian Birr, /fifty thousands Birr/.

b. regarding immovable property where the amount involved exceeds 100,000 Ethiopian Birr. /One hundred thousands Birr/.

9. ስለ ወረዳ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የወረዳና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በየበኩላቸው በፍትሐብሔርና በወንጀል ችሎቶች ይደራጃሉ።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቶቹ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ ለተወሰኑ ጉዳዮች ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጁ ይችላሉ።
3. በእያንዳንዱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀልም ሆነ የፍትሐብሔር ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ።

10. ስለ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አደረጃጀት

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉት ችሎቶች ይኖሩታል፦
   ሀ/ የፍትሐብሔር ችሎት
   ለ/ የወንጀል ችሎት
   ሐ/ የሰበር ሰሚ ችሎት
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽና ቀልጣፋ

Article 9. Organizational Structure of the Woreda and High Court

1. The Woreda and the High Courts shall have civil an criminal divisions.
2. Without prejudice to sub article 1 of this article, the courts. may have additional divisions, where necessary, having regard to accessibility and efficiency.
3. There shall sit one presiding judge and two other judges in each civil and criminal divisions in the High Courts.

Article 10. Organizational Structure of the Regional Supreme Court

1. The Regional Supreme Court shall have:
   a. civil division;
   b. criminal division; and
   c. cassation division.

2. Without prejudice to sub article 1 of this article , the Supreme Court may have additional divisions, where necessary, having regard to accessibility and efficiency.

ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለተወሰኑ ጉዳዮች ተጨማሪ ችሎቶችን ሊያደራጅ ይችላል።

3. በእያንዳንዱ የፍትሐብሔርና የወንጀል ችሎት አንድ ሰብሳቢና ሁለት ዳኞች ሁነው ያስችላሉ፤ ሆኖም በሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስችሉት አንድ ሰብሳቢና አራት ዳኞች መሆን ይኖርባቸዋል።

3. There shall sit one presiding judge and two other judges in each civil and criminal division;. However, there shall sit one presiding judge and four other judges in the cassation division.

4. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ወይም ምክትል ፕሬዝዳንት በማናቸውም ችሎት ሰብሳቢ ዳኞች ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ።

4. The President and Vice President of the Supreme Court may preside over any division.

5. በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት አጣሪ ችሎት ከቀረበ በኋላ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ ብይን ሲሰጥ ይሆናል።

5. A decision shall be heard in cassation where there is a belief that there exists a fundamental error of law as per the prior ruling of a screening bench wherein three judges of the regional Supreme Court sit.

11. <u>ስለ ይግባኝ ስርዓት</u>

በማናቸውም ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ከቀረበና ከተመረመረ በኋላ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ ይግባኙን ላቀረበው ወገን የመጨረሻ ይሆናል።

Article 11. Right of Appeal

Judgments once appealed shall be final as regards the appellant.

ሐ/ የአዋጁ አንቀጽ 8/ እንደተሻሻለ 12 /ንዑስ አንቀጽ /4/ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

/4/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /3/ የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ የክልሉ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽና ውጤታማ በማድረግ ዓላማ ላይ ተመስርቶ እንደአስፈላጊነቱ በስልጣን ክልሉ ውስጥ ዳኞችን በማዘዋወር ወይም በማናቸውም ስፍራ ቋሚ ችሎት በማደራጀት ሊያስችል ይችላል።

መ/ በአዋጁ ከአንቀጽ 22/ እንደተሻሻለ 27 /ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ/23/ የገባ ሲሆን ቀሪዎቹ አንቀጾች በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ መግባት ምክንያት አንቀጽ 28፣29፣ እና 30 ሆነው ተሸጋሽገዋል፣

/23/ በፍርድ ስራዎች ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታና ስለሚካሄድ ምርመራ

1. የዳኝነት ስራዎች ቅሬታ ሰሚ እና አጣሪ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ይደራጃል፣ ዳኞች እና አግባብ ያላቸው ሙያተኞችም ለስራው ይመደባሉ።

C. Article 8 (4) /as amended Article12/ is deleted and replaced by the following new sub- Article 8 (4)

(4) Without prejudice to the preceding sub articles the Supreme Court may arrange permanent benches in places other than the normal place of hearing having regard to accessibility and efficiency.

D. Article 22 /as amended Article 27/ is deleted and is replaced by the following new Article 23 while the articles following it are renumbered as Articles. 28, 29 and 30 in their order:

Article 23 Judicial Inspections on the complain of

Judgment

1. Judicial Inspections office shall be established in the Regional Supreme Court and High Courts; and it shall be staffed with Judges and other relevant professionals whose professions will conform with the duties bestowed to the office.

2. የፍርድ ስራዎች ቅሬታ ሰሚ እና አጣሪ በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚነሱና ከዳኝነት ስራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የብቃት ማነስ ወይም የስነ-ምግባር ጥሰት ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ያጣራል፣ ጉዳዩ በዲስፕሊን የሚያስጠይቅ መስሎ ከታየው ምክንያቱን በመዘርዘር ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ያቀርባል።

2. It shall examine grievances regarding judicial services, competence, disciplinary problems and shall, therefore, report its findings to the Judicial Administration Council where it is of the opinion that there are good reason to proceed.

3. በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት ከመፈፀም ጋር የፍርድ ስራ ቅሬታ መርማሪ እና አጣሪ በዳኝነት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በማጥናት የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

3. In addition, it shall conduct research on its own motion with a view to enable it to discharge the duties bestowed to it in order to enhance the judicial service. It shall also perform other duties as assigned to it by the President of the Court.

4. ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ማንኛውም ወገን በዚህ አንቀጽ መሰረት በፍርድ ስራዎች ላይ ቅሬታ የሚያቀርበው ባለቀላቸውና ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ ብቻ ይሆናል።

4. Without prejudice to the preceding sub articles, grievances shall be communicated to the office when the cases have acquired finality in the judicial process.

3. <u>በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች</u>

ይህ አዋጅ በጸደቀበት ወቅት በማንኛውም እርከን ባለ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ ፍፃሜ ያገኛሉ።

4. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሚያዝያ **29** ቀን **2002** ዓ.ም

አያሌው ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

3. Pending Cases

Pending cases prior to the coming into force of this proclamation shall continue to be tried by the laws applicable thereon.

4. Effective date

This Proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazzete of the Regional State.

Done at Bahir Dar,

This 7th day of May 2010.

Ayalew Gobezie

President of the Amhara National Regional State